# ታሪክ አጉዳፊ ታሪክ ጸሐፊዎች፤

በመሰረቱ ታሪክ ሲባል እኔ እንደሚገባኝ ባንድ ወቅት በግለሰብ ይሁን በቡድን ወይም በሃገር ደረጃ የተፈጸሙ ፍጻሜዎች አጀማመራቸው ሂደታቸው እና ፍጻሜአቸው ሳይዛባና የግል ስሜት ሳይገዛው እውነታን መሰረት አድረጎ የሚቀርብ ነው። እውነታን መሰረት አድርጎ ተጨባጭ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሚጻፍ ታሪክ ለቀጣይ ስራዎች ይሁን ለቀጣይ ትውልድ እንደ መረጃ ሆኖ ባስተማሪነት የሚቀርብ ይሆናል። ማነኛውም የታሪክ ጽሑፍ በምንም መልኩ ባዎንታም ይሁን ባሉታዊ መልኩ በከፊልም ይሁን በሙሉ ከነበረው እውነታ ዝንፍ ካለ ታሪክ መሆኑ ያቆማል፤ ከዚያም አልፎ ከአስተማሪነቱ ይልቅ አፍራሽነቱ ያመዘነ ይሆናል።

አገራችን ኢትዮጵያን በተመለከተ ብዙ ያገር ውስጥና የውጭ አገር ታሪክ ተመራማሪዎች በስፋት ጽፈውበታል።ሁሉም የታሪክ ጽሑፎች ምንም እንከን የሌላቸው ፍፁም ናቸው ባይባሉም ከእውነታው ጋር ያላቸው መቀራረብ ግን እንደየጸሐፊዎቹ ይለያያል።አንዳንድ ጸሐፊዎች ለሞያው ካላቸው ክብር ተነስተው በተቀነጫጨበ መረጃ ወይም በስሜት ተገፋፍተው ሳይሆን ዝግጅት አድርገውበት አስፈላጊ ናቸው ያልዋቸው መረጃዎች በማሰባሰብ መጥፋት ያለበት ጊዜ ካለም ጠፍቶበት ከስሜታውነት ነፃ ሆነው በወቅቱ የተፈጸሙ ፍጻሜዎች እንዳሉ አድርገው ስለሚጽፉዋቸው ጊዜ የማይሽራቸው መረጃና ቅርስ ሆኖው ይኖራሉ። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች የሚጽፉዋቸው በስሜት ተነሳስተው ሊያጣጥሉት የፈለጉትን ለማጣጣል ሊክቡት የፈለጉትን ለመካብ በሚያመቻቸው መንገድ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ለሚያራምዱት የፖለቲካ እምነት ፍጆታ ሆኖ እንዲያገለግላቸው መነሻ በማድረግ ነው።እነዚህ መጻህፍት ደግሞ ከአስተማሪነታቸው ይልቅ አደናጋሪነታቸው፤ከገንቢነታቸው ይልቅ አፍራሽነታቸው ያመዘነ ይሆናል።

ለዚህ ጽሁፌ ዋነኛ መነሻ ሁሉንም የታሪክ ጸሐፍት ለመገምገም ሳይሆን ባሁኑ ጊዜ ታሪክ እንፅፋለን እያሉ እውነተኛውን ታሪክ በማዛባት፤ ሊያስተላልፉት የፈለጉትን መልእክት ያጠናክርልናል ያሉትን ፈጥረው በመጨመር ምንነቱ የማይታወቅ ፅሁፍ በብዛት እየተሰራጨ ያሉትን ነው።

ለዚሁ ፅሁፌ እንደ መጣቀሻ የምጠቀምበት መፅሓፍ በሻለቃ ዳዊት ወልደጊወርጊስ የተፃፈ "ክህደት በደም መሬት" የሚለውን

መጽሐፍ ነው። ይህን መጽሐፍ የመረጥኩበት ሻለቃ ዳዊት “ቀይ እንባ” በሚለው መጽሐፋቸው ስለማውቃቸው ያንን የሰላ ብእራቸው አሁን በጻፉት “ክህደት በደም መሬት” በሚለው መጽሐፋቸው ፈትሼ ላገኘው ስላልቻልኩ ነው ፤ እንጂ ከዚህ የባሰ መተቸት የሚገባው የታሪክ መጽሐፍ ተብዬ ጠፍቶ አይደለም። ለምሳሌ በአቶ ተክሌ የተደረሰው “የኢትዮጵያ አንድነትና የትግሬዎች የስልጣን ሽሚያ” እንደአብነት መውሰድ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነቱ መጻሕፍት መተቸት ሳይሆን ከተቻለ ተከታዩ ትውልድ ሳይበክሉ ተሰብስበው መቃጠል የሚገባቸው ናቸው።

ሻለቃው ዳዊት ይህን ፅሁፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳቸው የታሪክ ተማራማሪ ስለሆኑ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው የፖለቲካ ትኩሳት ነው። ስለዚህ መጽሀፉ ከጥንስሱ ጀምሮ የራሳቸው የፖለቲካ እምነትና አመለካከት ያጠላበት እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይሆንም። መጽሐፉ ደጎስ ያለ በመሆኑና ርእሱም እንድታነበው የሚጋብዝ ነው። በመሆኑም ነው እኔም መጽሐፉን ለማንበብ የበቃሁት። የመጽሐፉ ውስጠ ይዘት ከመጀመሪያው ጀምሮ እውነተኛውን ታሪክ እንደ ታሪክ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ያቀደ ሳይሆን ጸሐፊው ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክት ለማስተላለፍ ተቃኝቶ የቀረበ ለመሆኑ በየምእራፉ ያስገቡዋቸው ማስረጃዎች አንዳንዶቹ ፈጠራ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የነበረውን እውነታ በማዛባት ለመጠቀም መፈለጋቸው ማስረጃ ነው።

አነሳሴ ሙሉውን መጽሐፍ ለመገምገም አይደለም።መጽሐፉ እንደትልቅነቱ በውስጡ ብዙ እውነታዎች አሉት።
ዋናው ትኩረቴ ሆን ተብለው ታሪክን ለማዛባት እንደ መረጃ ባስቀመጥዋቸው ላይ ይሆናል።

1- በመቅድሙ ላይ አንድ ትልቅ እውነታ አስቀምጠዋል። …” *ያለንበት ዘመን አደገኛ ነው።እውነተኛ ታሪክ እየተፋቀ፡ አዲስ ታሪክ እየተፈጠረ ነው።ታሪክ ሰሪው ህዝብ ነው። ታሪክ ጸሐፊው ግን አሸናፊውና ገዢው ክፍል ሆኖዋል።የገዢዎች ዘመን እየተራዘመ ሲሄድ በዚያው መጠን የሐሰት ትረካቸው ስር እየሰደደ ይሄዳል። ….. ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የፈጠራ ታሪክ እውነት ትሆናለች፤”* ይላል። በመሰረተ ሃሳቡ ብስማማም ይህች አባባል ለገዢው ክፍል ብቻ የምትሰጥ ሳይሆን ከየትም ይሁን ማለት ከአሸናፊም ይሁን ከተሸናፊ ወይም ገለልተኛ ወረቀት ላይ ታሪክ ነው ብሎ ለሚያሰፍር ሁሉ የምትመለከት ናት። ስለዚህ ሻለቃ ዳዊትንም ራሳቸው ባስቀመጥዋት መሰረተ ሐሳብ መነሻ በማድረግ እነዚህ በጭብጥነት ያስቀመጥዋቸው ግን ከእውነታው

በጣም የራቁ ጊዜ በወሰዱ ቁጥር ሃቅ እየመሰሉ ስለሚሄዱ በወቅቱ መስተካከል ስላለባቸው ነው።

2- መግቢያ ላይ ሻለቃ ዳዊት ከወጣትነት እድሜ እስከ ጉልምስና እድሜያቸው ኤርትራ ውስጥ እንደነበሩና በተለያዩ ወታደራዊና ሲቪላዊ ስራዎች በወቅቱ አገራችንን ሲገዙ በነበሩት መንግስታት በሚሰጥዋቸው የሃላፊነት ቦታና በሚሰጥዋቸው መመሪያዎች ሲያገለግሉ እንደነበረ ገልጸዋል።እሳቸው ግን በገጽ 4 *“በቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዘመንም ሆነ በደርግ ጊዜ የኤርትራን ሕዝብ ለማገልገል እድል በማግኘቴ”* በማለት ይጀምራሉ።ከዚህ ነው የሻለቃ ዳዊት ታሪክን በታሪክነቱ እንደማስቀመጥ መበረዝ የሚጀምረው።ሻለቃ ዳዊት ኤርትራ የተመደቡት እሳቸው እንዳሉት የኤርትራን ህዝብ ለማገልገል ሳይሆን  የነበረውን ስርዓት ለማገልገል ነው።ሁለቱ አባባል መሰረታዊ ልዩነት አለው። ይህችን ሐረግ ትኩረት ልሰጥባት የፈለኩት እንዲሁ ባጋጣሚ የገባች ሳይሆን ቀጣይ ትረካቸውን መልክ እንድታሲይዝላቸው ብለው ስለከተትዋት ነው።ይህ ምንም ክርክር የማያስፈልገው ቁልጭ ያለ ሃቅ ነው። የነበሩት ስርዓቶች ደግሞ ጸረ-ዴሞክራሲ መኖራቸው ራሳቸው ሻለቃ ዳዊትም አይክዱትም። ስለዚህ አንድ ጸረ ዴሞክራሲ የሆነ መንግስት ለዚያውም መረጋጋት በሌለበት አካባቢ ወታደራዊ መኮንኖች፡ አስተዳዳሪዎች፡  የፖለቲካ ሐላፊዎች ሲመድብ ዴሞክራቲክ እና ሰብአዊ በሆነ አገባብ ችግሩን እንዲፈቱ ተቀዳሚ ዓላማው አድርጎ አይደለም።ወደዱም ጠሉም አንገታቸው ረግጠው አሜን ብለው እንዲገዙ መጠቀም የሚችሉትን ሁሉ ተጠቅመው እንዲያስተዳድሩላቸው ነው።ታድያ ከዚህ መርህ ውጭ በየትኛው መመዘኛ ነው እሳቸው ኤርትራ ውስጥ በተለያዩ ሐላፊነት በነበሩበት  ጊዜ የስርዓቱ ቁንጮ ከነበሩት ከአጼ ሐይለስላሴ ቀጥሎም  ከኮሎኔል መንግስቱ መርህ ውጭ ከሰማየ ሰማያት የኤርትራን ህዝብ ለማገልገል(ለማዳን) የተላኩ መስለው ለመቅረብ የሚፈልጉት። ሻለቃ ዳዊት በወጣት መኮንንነት ኤርትራ በነበሩበት ጊዜ ካስታወሱት ሲሰራ የነበረው በደጋው በጋብቻና አምቻ አልፎም በአንዳንድ ጥቅማጥቅም ግለሰቦችን ለመያዝ ከመጣር ባሻገር መሰረታዊ የሆነ የችግሩ መንስኤ አጥንቶ ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣ ተግባር አልተሰራም፤በቆላው አከባቢ ደግሞ ለወንበዴ ተባብረሃል እየተባለ በላዩ ላይ  ሲፈጸም የነበረው አሰቃቂ ግፍ የሚያወሐህድ ሳይሆን በከረረ ጠላትነት ተፈራርጀህ በጥርጣሬ እንድትተያይ የሚያደርግ ፍጻሜ እንደነበረ ሻለቃ ቢክዱትም በወቅቱ

ወታደራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ከነበሩት የ10ኛና የ35ኛ ሻለቃ አባላት ህያው ምስክሮች አሁንም አሉ።የኤርትራ ጉዳይ በሁለት ሶስት ገጽ ለመግለጽ የማይደፈር ቢሆንም ጠቅለል ባለ መልኩ ግን ከአጼ ምኒሊክ ጀምሮ አሁን እስካለው ገዢ ፓርቲ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. በየደረጃቸው በፈጸሙዋቸው ስህተቶች ድምር የተገኘ ውጤት ነው። ይህ ሐቅ ቢጎመዝዝም የታሪክ ሐቅ ነውና እየጎመዘዘን መቀበል የግድ ይላል። አለበለዚያ አጼ ምኒሊክን እንደ መልአክ የሚያመልክ ባንድ ወገን፤አጼ ሃይለስላሴን እንደጣኡት የሚሰግድላቸው በሌላ ወገን፤ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን አትንኩብኝ የሚለው ባንዱ ወገን አካኪ ዘራፍ ቢሉ እውነተኛውን ታሪክ ከመበረዝና ከማዛባት አልፈው ያመጡት ውጤት የለም ወደፊትም የሚያመጡት ውጤት ፈጽሞ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም በአንድ ወቅት የተፈጸመ ፍጻሜ አስተማሪ ሊሆን የሚችለው ጠንካራም ይሁን ደካማ ጎኑ ሳይዛባና ሳይበረዝ ሲቀመጥ እንጂ ያልነበረ ነበረ እያልክ የነበረው ስላልጣመህ እየቆረጥክ መጣል ከተጀመረ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ይሆንና ግብ የሌለው መባከን ብቻ ይሆናል። የሻለቃ ዳዊት መጽሐፍ "ከህደት በደም መሬት"ም በዚህ ቅኝት ስለተጉዋዘች ከህልም የዘለለ ተጨባጭ ግብ አይኖራትም።

3- ስለ የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ልዩነት የለንም። ልዩነታችን በኢትዮጵያ በተለያየ ጊዝያት የመጡ መሪዎች አንዱ ካንዱ ሳይማር ስሜታቸው በገፋቸው መንገድ ብቻ ችግሩን ለመፍታት ባደረጉት እንቅስቃሴ ነው።
ዘውዴ ረታ በመጽሐፋቸው አጼ ሀይለስላሴ የኤርትራ ችግር አጼ ምኒሊክ ያወረሱን ችግር ነው እያሉ ያማርሩ እንደነበር ገልጸውታል።አጼ ምንሊክ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፤ወደውም ይሁን ተገደው ብዙ አከራካሪ ቢሆንም ለኤርትራ ችግር መነሻ መሆናቸው ለመግለጽ ያሉት እንደሆነ ግልጽ ነው። አጼ ሀይለስላሴም የኤርትራ ችግር ለመፍታት ከፌደረሽን በፊትና ከፌደሬሽን መፍረስ በሁዋላ በኤርትራ ውስጥ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ሳይሆን የራሳቸው ስሜትና ፍላጎት የገዛው ስለነበር ምንም ለውጥ ሳይኖር በአንጻሩ ኤርትራዊያን ኤርትራዊነታቸውን እንዲያጣጥሙ "ለነጻነታቸው" በጽናት እንዲቆሙ አድርጎ እንዳለ እዳው ለደርግ ሊተላለፍ ችለዋል። ይህን ለመገንዘብ ብዙ ሳንጉዋዝ የዘውዴ ረታ "የኤርትራ ጉዳይ" የሚለውን መፅሐፍ ማንበብ በቂ ይመስለኛል። ደርግም በወገኑ በከፋና በባሰ መልኩ በጭካኔ ወደር የሌለበት እረደው፤ገደለው

የሚል መፍትሄ ነው የተከተለው። የደርግ ፖሊሲ በኤርትራ ሁኔታዎችን አባባሰ እንጂ አላረገበም። አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስትም ከመጀመሪያው ጀምሮ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የነበረው አቋዋም ችግር ያለበት፤ስልጣን ላይ ከወጣ በሁዋላም በአፈታቱ ላይ የተከተለው ስልት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ማንነት ግምት ውስጥ ያላስገባ ልክ እንዳለፉት መሪዎች በድርጅታዊ ስሜትና ፍላጎት እየተነዳ የወሰደው እርምጃ በመሆኑ አሁንም የእግር እሳት ሆኖ እንዳቀጠለ ነው። ስለዚህ ስለ ኤርትራ ስናነሳ መጀመሪያ ምንም ሳይዛነፍ የነበረው ጥሬ ሃቅ ማስቀመጥ፤ቀጥሎ በዚህ ሃቅ ውስጥ ቁልፍ ችግሩ ምን እንደነበር በትክክል ለመፈተሽና ተገቢውን መፍትሔ ለማስቀመጥ አመቺ ይሆናል።ከዚህ በመለስ ሓቁን ከሽፋፈን ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ሆኖ ይቀራል። ያለፉት ስርዓት አካሔድም ትክክለኛው የችግሩ ታሪካዊ አመጣጥ ወደጎን በመተው ራሳቸው በሚፈበርኩት ታሪክ ውስጥ የችግሩ መንስኤ ለመዳሰስ ሲሞክሩ የሚታያቸው እውነተኛው የችግሩ መንስኤ ሳይሆን የፈጠራ ታሪኩ ውጤት የሆነ መንስኤ ነው። መፍትሔው ተጨባጩ ሁኔታ ያላገናዘበ ስለሚሆን ውጤት አልባ ይሆናል። በአለፉት ዓመታት ያየነውም ይህን ነው።

ሌላው በዚሁ መግቢያ ጽሁፋቸው በገጽ 8 ላይ የኢትዮጵያ ነጻ ወታደሮች ንቅናቄ (ኢ.ነ.ወ.ን) በሚል እንቅስቃሴ እንደጀመሩ፤ከሻእቢያ እና ከወያኔ አመራር ጋር በተደጋጋሚ እንደተወያዩ፤ በተለይ ከሻእቢያ አመራሮች ጋር ሳሕል ድረስ ተጉዘው እንደነበርና ከሻእቢያ ጋር የሆነ ስመምምነት ተደርሶ እንደነበር፤ ወያኔ ግን በመጀመሪያ እያመናታ በመጨረሻም እንዳልተስማማ፤ በማህልም መፈንቅለ መንግስቱ እንደከሸፈ፤ቀጥለውም ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. አዲስ አባባን ለመያዝ ሲገሰግስ ባለበት እንዲቆምና የተኩስ ስምምንት እንዲደረግ ጥረት ማድረጋቸው፤ ይህንን ሳይሳካ በመቅረቱና ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. መላው አገሪቱን ስለተቆጣጠረ ፖለቲካን እርም ብለው እንደተዉት ገልጸዋል። ለምን?

ሻለቃ ዳዊት ኢ.ነ.ወ.ን. የተባለ የወታደራዊ መኮንኖች ስብስብ ይዘው በኢትዮጵያ ውስጥ በእርሳቸው ሊቀመንበርነት የሚመራ ጊዝያዊ መንግስት(ሻእብያና ወያኔን ያካተተ) ለመመስረት ሲያልሙ የሻእብያን ባላውቅ ወያኔ ግን ከወታደር ወታደራዊ አስተዳደር እንጂ መሰረታዊ ለውጥ ሊመጣ አይችልም የነሻለቃ ዳዊት ለማዘናጋትና ጊዜ ለመግዛት የሚደረግ ሸር ጉድ ነው፤ብሎ በአንድ በኩል በግልጽ ሲያስቀምጥ በሌላ በኩል ደግሞ ሳንሸፋፍን

እናስቀምጥ ካልን አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ ደም የከፈለበትን ፖለቲካዊ ስልጣን የመያዝ እቅዱ በብልጣ ብልጥነት በቦሌ ሊቀድሙት እንዳሰቡ ቀድሞ ስለነቃባቸው ሐሳባቸውን ሊቀበለው አልቻለም። ምክንያቱም ወያኔ ራሱ የሚመራው የሽግግር መንግስት እንጂ ሌሎች በሚያቋዋቁሙት ገብቶ መጨረሻ ወደሌለው ጉዞ ሊገባ አልፈለገም።የፖለቲካ ስልጣን የመያዙ እድል 95% እርግጠኛ በሆነበት በ11ኛው ሰዓት አቁምና እኔ ልምራህ ሲባል ባለማቆሙ ሳይሆን መተቸት የሚገባው ቢያቆም ኑሮ ነበር። እንደ አግባቡ ከሆነ የሻለቃ ዳዊት ድርጅት ነበር ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. በሚመሰርተው የሽግግር መንግስት መግባት የነበረበት። በዚህም አላቀመም ለኢ.ነ.ወ.ን. ታማኝ የነበረ ለወያኔ ግን የጊዜ ፈንጂ ሊሆን ምንም ጥርጥር ያልነበረው ሰራዊት ከነአለቆቹ ሲበትን ፖለቲካን እርም ማለታቸው ብዙ የሚያስደንቅ አይደለም። ሌላው ሻለቃ ዳዊት ከልባቸው ይሁን ለፖለቲካ ፍጆታ ብለው ወያኔ በሻእብያ የተፈጠረ ለሻእቢያ የቆመ ሲሉት የነበረ እውነት አድርገው ስለወሰዱት ቀድመው ከሻእብያ ጋር ነው ለድርድር የተቀመጡት። ሻእብያ ከተስማማ ወያኔ ይከስማል የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ የፈጠረው ነው። አግባብ የነበረውማ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የነበሩ ተቀዋሚ ሐይላት ባንድ ተሰባስበው በኢትዮጵያ ውስጥ የሰከነና የተረጋጋ ሁኔታ በፍጠር መሆን ነበረበት። ሳሕል ላይ ቆመህ ነው የሚመቸው ወይስ መሐል ኢትዮጵያ? የተሳሳተ ታሪክ(መረጃ) ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ያመራህና ወደ ተሳሳተ መፍትሄ ወስዶ ይዘፍቀሃል።

በገጽ 15 ላይ "…. *ሻእብያ በኢትዮጵያ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለማደራጀት ብዙ ሰረተዋል።ሕ.ወ.ሓ.ት. የተቋዋቋዋመው፤የሰለጠነውና የተደራጀው በሻእብያ ነው።ኦ.ነ.ግ. የተቋዋቋዋመው፤የተደራጀውና የሰለጠነው በሻእብያ ነው።የምእራብ ሱማሌ ንቅናቄ የተደራጀውና የታጠቀው ከሻእብያ ባገኘው እርዳታ ነው።…..*" በማለት እነዚህ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠሩ የቻሉበት ነባራዊው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከታሪክ ፍቀው በማውጣት አዲስ ታሪክ እየፈጠሩ እንደሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ወታደራዊ ሐይሉ አጼ ሃይለስላሴን ሲገለብጥ የሻእብያ ፍላጎት ስለሆነ ነው? ወይስ በኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የነበረው ብሶት? ኢ.ህ.አ.ፓ ለምን እንደተወ.ት አልገባኝም ኢ.ህ.አ.ፓም የሰለጠነው በሻእብያ ነው፤አዲስ እየፈጠሩት ላለው ታሪክ እንደማያጠናክርላቸው ስለገባቸው ይመስለኛል፤ መ.ኢ.ሶ.ን. ሌሎችስ በሻእብያ ድጋፍ

ነው? ሻለቃ ዳዊት በመቅድሙ ያስቀመጡት መሰረተ ሐሳብ ለይስሙላ አስቀመጡት እንጂ ላጠቃላይ ትረካቸው መሪ ቃል ሆኖ ሲገራቸው አይታይም። በኢትዮጵያ የተፈጠሩት እንቅስቃሴዎች በሀገሪቱ ሰፍኖ የነበርው አስከፊ አገዛዝ የወለዳቸው እንጂ ሻእብያ የፈጠራቸው አይደሉም።ራሱ ሻእብያም የተፈጠረው የአጼ ምንሊክና የአጼ ሃይለስላሴ ባጠኣላይ በኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ በኤርትራ በነበራቸው የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ነው። ሁላችን እንደምናውቀው በኢትዮጵያ የአጼ ሃይለስላሴን ስርዓት የሚቃወሙ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። በተለይ በዩኒቨርሲቲና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጠንከር ባለ መልኩ ነበር።ስለዚህ እነዚህ በኢትዮጵያ የተፈጠሩ የፖለቲካ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲ የነበረ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጥንስስ ውጤቶች ናቸው። በወቅቱ በአካባቢው የትግል ልምድ የነበረው ሻእብያ ስለሆነ የዚህ ድርጅት አጋርነትና ድጋፍ መጠየቅ ባህሪያዊ ነው።ሻእብያ ለራሱ ጥቅም ድርጅቶቹም ለጥቅማቸው ብለው ያደረጉት መቀራረብ ነው።እንኳዋንና በዚያን ጊዜ አሁንም ያሉት ተቀዋሚ ድርጅቶች ያንን ስልት እየተጠቀሙበት ነው። ድርጅቶቹ ደግሞ ከዚህ የዘለለ የፈጸሙት የለም። በሁዋላ ሻእብያ ተጽእኖ በማድረግ እንደመሳሪያነት ለመጠቀም ያደረገው እንቅስቃሴ እንደየድርጅቶቹ ይለያያል። አንድ ነገር ለማለት ግን ህ.ወ.ሓ.ት. የሻእብያ መሳሪያ ቢሆን ኑሮ ሻእብያ የሻለቃውን ሐሳብ ተኩስ የማቆም ስምምነት ሲቀበል ወያኔ ስምምነቱ ሳይቀበል በመቅረቱ እቅዳቸው እንደከሸፈ ራሳቸው ያስቀመጡት ጭብጥ ነው። ለዚህ ነው ታሪክ በታሪክነቱ ሳይዛነፍ መዘገብ አለበት እንደ መሳሪያ ሊጠቅምህ ከሆነም ሐቀኛ ታሪክ ከሆነ እንጂ ከተዛነፈ መንገድ እንድትስት ያደርግሃል፤መንገድ ከሳትክ ደግሞ መድረሻህ በትክክል አታውቅም። ሻለቃ ዳዊት ለትረካቸው እንዲያጠናክርላቸው አዲስ የፈጠሩት ታሪክ ደግሞ ግለ ሰቦችን የሚመለከት ነው።በገጽ 14 “ *....መለስ (ለገሰ) ዜናዊ እ.ኤ.አ. በ1974 እና በ1975 ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ወጥቶ የሚኖረው በአስመራ ከተማ ነበር።ለሻእብያ አባልነት የተመለመለው አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ በነበረበት ወቅት ነው። አስመራ ከተማ ሆኖ የሻእብያ መዋቅር (ሴል) አባል ሆኖ ወረቀት በመጻፍ፤ በመበተንና ወጣቶች በመመልመል ብዙ ተግባራት ፈጽመዋል።...... በደርግ ጊዜ በቁጥጥር ከዋለው የሻእብያ አባል የምርመራ ቃል ለመረዳት ተችለዋል።*” ይሉና በመቀጠል የሌሎችን ስም ዝርዝር በመጥቀስ የሆና ያልሆነ የዘበራረቀ የግለ

ሰዎችን ስብእና ለሳቸው በሚያመቻቸው ሲያሸሞኖሙኑት በጣሙን አስገራሚ ግን ሳሞራ የኑስ አክሱም ተወልዶ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ በረሃ እስከወጣበት ድረስ እዛው አክሱም ያደገ ሲሆን እሳቸው ግን በገጽ 18 *“ሳሞራ የኑስ አሁን የመከላከያ ሰራዊት ኤታማዦር ሹም ሲሆን አስመራ የተወለደ ያደገ ሙሉ ለሙሉ ኤርትራዊ ነው።እኔ ኤርትራ በነበርኩበት ጊዜ ገዛ ብርሃኑ ሸማኔ (በትግርኛ አላማይ) የነበረ ነው።”* ብለውን እርፍ። እነዚህ ተራ ግድፈት አይደለም፤ ልክ ለአቶ መለስ እንደፈጠሩላቸው ታሪክ በአንድ ወቅት የተማረከ የሻእብያ አባል እንደሰጠው የምርመራ ቃል በሚል ፈሊጥ ሳይሆን እሳቸው ኤርትራ በነበሩበት ወቅት ገዛ ብርሃኑ ውስጥ ሸማኔ እንደነበር አስረግጠው እየነገሩን ነው። ምናልባት በዚያን ወቅት ጋቢ ሰረቶላቸው ይሆን። ለመሆኑ ሳሞራ ሸመና ይችላል ወይስ እስላም ስለሆነ ያባት ነውና መቻሉ አይቀርም ብለው ነው። ማኝኛውም በአክሱም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለፈ ቢጠየቅ በቀላሉ ሊመልሰው ስለሚችል እዚህ ላይ ብዙ ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም። ስለ አቶ መለስም እንዲሁ በ1974ነ1975 አዲስ አባባና ዓድዋ አብረው የነበሩ አሁንም በሂወት ስላሉ ብዙ የሚያከራክር አየደለም ፤ “ብትበርም ፍየል ናት “ እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር። የሻለቃው ዋና ግብ ህ.ወ.ሓ.ት. በሻእብያ የተፈጠረ ለሻእብያ የቆመ፤ በኤርትራ ለተፈጠረው ችግር ዋነኛ ተጠያቂ ነው ማለት ለፈለጉት ድምዳሜ ያጠናክርልኛል እስካሉ ድረስ ዓይናቸው በጨው ታጥበው በፈጠራ የታጀበ (ለዚያውም ደሮ ጭራ ለምታገኘው) አዲስ ታሪክ እየሰሩ ለመሆናቸው መነገር ይገባቸዋል።

በሻለቃው ዓይነት አስተሳሰብ የሚነዱ ኤርትራዊያንምኮ በኤርትራ ከፕሬዚዳንቱ ጀምሮ በከፍተኛ ስልጣን ላይ ያለው ቡድን ኢትዮጵያዊ (የትግራይ ተወላጅ) ነው ይሉታል። እንዲያውም ሻለቃው ካቀረቡት መረጃ የበለጠ አላቸው። ይህ ዓይነት ግምገማ ግን የትም የሚያደርስ አይደለም። ዋናው አመለካከታቸውና እምነታቸው ነው ወይስ ዘራቸው ነው በሚያራምዱት ፖለቲካ ቀድሞ መታየት የሚገባው። መለኪያችን ዘር ከሆነ ብርሃነ መስቀል ረዳ፡ ተስፋይ ደበሳይ፡ ዘርኡ ክሕሸን፡በረከት ስምኦን ከኢህአፓ ባልተሰለፉ። ዋናው መለኪያ የፖለቲካ አመለካከት ስለሆነ የፖለቲካ አመለካከታችንን ይወክልናል ካሉት ድርጅት ለመሰለፍ ቻሉ። ይህን መሰረተ ሐሳብ ደግሞ በሁሉም እኩል የሚሰራ ነው።

4-በምዕራፍ 10 ገጽ 175-176 ላይ በዶክተር ተወልደ ትኩእ እና በፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ኤርትራን በተመለከተ እንደ ታሪክ ተማራማሪነታቸው የደረሱበትን የታሪክ ሃቅ በጣም ስለጎመዘዛቸው ለመቀበል እንደተናነቃቸው በግልጽ ይታያል። አንባብያን ግልጽ እንዲሆንላችሁ የሁለቱም የታሪክ ምሁራን አስተያየት እንደሚከተለው ይላል።

ከዶክተር ተወልደ የተወሰደው

*"በታሪካችን የሀፍረት ማቅ የተከናነበ፤በክህደት ከታሪክ የማይፋቅ አሳፋሪ ተግባር በመስራት የሀገሩን ህዝብና መሬት የሸጠ አጼ ምንሊክ ነው።.......በዘመናችን የታሪክ ክህደት ምንጩም ዋና ባንዳ አድርገን የምናውቀው ምንሊክ ብቻ ነው።...የኤርትራ ነጻ ሀገር መፈጠርም የምንሊክ ክህደት ያመጣው ነው።"*

ከፕሮፌሰር ባሕሩ የተወሰደው

*"ይሁን እንጂ በፖለቲካ ረገድም ሆነ ከግዛትዋ ይዘት አንጻር ዓድዋ ለኢትዮጵያ ፍጹም ነጻነትን አረጋግጣለች ለማለት ያዳግታል።በ1892 የመረብ ወንዝ የኤርትራና የኢትዮጵያ ድንበር መሆኑ በውል ሲደነገግ ታሪካዊ የሰሜን ግዛትዋ አስረከበች።ኢጣልያ በጦር የያዘችው ግዛትም በሕግ ጸደቀላት።ይህ ሁኔታ ምናልባት የዓድዋ ድልና የምኒልክም ፖሊሲ ከፍተኛ ድክመት ነበር ተብሎ ሊታሰብ ይገባል።"*

እነዚህ የታሪክ ምሁራን ወደዚህ ድምዳሜ የደረሱት በወቅቱ ከነበረው የዓለም ፖለቲካና የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተው ነው።

ሻለቃ ዳዊት ይህን እውነታ መቀበል ስላልፈለጉ ታሪክን ወደማውገርገር ይገባሉ። በገጽ 176 እንዲህ ይላሉ፤

*"ወደ ሁዋላ ዞር ብለን በጊዜው የነበረውን ሁኔታና እዚህ ውሳኔ ላይ ያደረሳቸውን ምክንያት ካልመረመርን አጼ ምኒልክን ማውገዝ ቀላል ነው።እንዲህ ከተባለ አጼ ዮሐንስም ከዚህ ወቀሳ አይድኑም። እንዲያውም ኤርትራን ለጣልያን ያስረከቡ አጼ ዮሐንስ ናቸው።አጼ ምኒልክ የደረሱት የራስ አሉላ ሰራዊት ከባሕር ጠረፍ ካፈገፈገ በሁዋላ ነው።"*

በማለት ስለ አጼ ዮሐንስ መጨበጫ መያዣ የሌለው ካንዱ ወደ አንዱ እየዘለሉ በዶክተር ተወልደና በፕሮፌሰር ባሕሩ የተቀመጠውን ሐቅ ለማጉደፍ ያቅማቸውን ብዙ ለማለት ሞክረዋል።እነዚህ የታሪክ ምሁራን ይህን ታሪክ ሲጽፉ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ መርምረው እንጂ እንዲሁ በግብታውነት አይመስለኝም።አለፍ ብለውም አጼ ዮሐንስ ከእንግሊዝ ጋር አብረው ለአጼ ቴድሮስ ጥፋት ምክንያት እንደሆኑ ሊያስተምሩን ይሞክራሉ። በነካ እጃቸው ግን አጼ ምንሊክ በአጼ ዮሐንስ ላይ ከጣልያን ጋር ሲፈጽሙት የነበርው አሳፋሪ ሴራና ዱለታ ምነው ሳይጠቅሱት አለፉ። ይሄ ራሱን የቻለ ሰፊ ታሪክ ስለሆነ መነካካት አልፈልግም ዋናው ጭብጤ እንዳያስተኝ።

ለእልሁ ካልሆነ በስተቀር አጼ ዮሐንስ ዋናው የጦር መሪያቸው ራስ አሉላ አስመራ ላይ የጦር ማዘዣቸው እንዲያደርጉ በማድረግ ጣልያንን መፈናፈኛ እንዳሳጡት ነው የሚታወቀው እንጂ ኤርትራን ለጣልያን አሳልፈው ሰጡ የሚለው ራሳቸው አጼ ምንሊክም ከመቃብር ተነስተው ቢሰሙት ይታዘብዎት እንደሆን እንጂ የሚደግፉት አይመስለኝም።

ታሪክ እንደሚያስታውሰው አጼ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት በነበሩበት አጼ ምንሊክ ንጉሰ ሸዋ እነንደነበሩ የሚታወቅ ነው።-አፄ ምኒልክ በዓድዋን ጦርነት ጣሊያንን ካሸነፉ በህዋላ መረብን ተሻግረው ኤርትራን ያለመቆጣጠራቸው አንድ ሆኖ እያለ በውል ሰነድ በተደገፈ ለጣልያን ፈርመው መስጠታቸው ሲተች ሓቁን እንደመቀበል ወይም አሳማኝ ነጥብ ካለ ደግሞ ያንን ጭብጥ ይዞ እንደመከራከር የማይገጣጠም ታሪክ አምጥቶ የሰውን ታሪክ ማጉደፍ ምናለባት ለታሪክ ፀሓፊው ያረካው እንደሆን እንጂ በምንም መመዘኛ ሊያሳምን የማይችል ጭብጥ ነው።

ምንሊክ በዚህ ከተወቀሱ ዋናው ተወቃሽ ዮውሓንስ መሆን አለባቸው ምክንያቱም መጀመሪያ ኤርትራ ለጣልያን የተዉለት ዮውሓንስ ናቸው፡ ጣልያንን እስከ መጨረሻ እንደመዋጋት እሱን ትተው ደርቡሽን ለመዋጋት ወደ መተማ በመውረዳቸው ሲሉ፤ እስቲ የነበረውና የተለያዩ የታሪክ ፀሐፊዎች ከፃፉት ብንነሳ በነበረው የስልጣን ፉክክር ከጣሊያን ጋር ተደጋጋሚ ስምምነት (በተለይ ዮውሓንስን ለማጥቃት) ሲያደርጉ የነበሩ ምኒልክ ናቸው። ዮውሓንስ ግን ምኒልክ ከጣልያን ጋር ሆነው ቢያስሩባቸው ኤርትራን ላለመስጠት ብዙ መስዋይትነት ከፍለዋል። በመጨረሻም በኤርትራ ጣልያን በጎንደር ደርቡሽ ሁለቱም የውጭ ወራሪዎች ባንድ ጊዜ ሲገጥማቸው ቅድሚያ

ላንዱ መስጠት ግድታ ሰለነበር ከነበራቸው የክርስትና ሓይማኖት አጥባቂነት ቤተ ክርስትያን እያቃጠለ ያለውን ደርቡሽ መጀመሪያ መደምሰስ እንዳለበት አምነው ወደ መተማ ለመዝመት ተገደዱ እንጂ ጣልያንን ችላ ብለው አይደለም። ከደርቡሽ መልስ ጣልያን ነበር: ህልማቸው ባጭሩ መተማ ላይ ቀረ እንጂ:: ዮውሓነስ ምኒልክ ሲክድዋቸው ጣልያንን በመተው ወደ ምኒልክ አልዘመቱም። ታድያ ሻለቃው ዮውሓንስ ጣልያንን ለጊዜው ትተው ወደ ደርቡሽ መዝመታቸው በየትኛው የኢትዮጵያዊነት መመዘኛ አይተው ነው ኤርትራን ለጣልያን አሳልፈው የሰጡ ዮውሓንስ ናቸው ለማለት የበቁት።

የጣልያን ወራሪ ሀይል በሰሜኑ ሲፈታተናቸው በመተማ በኩል ደግሞ ደርቡሽ ሁኔታዎችን ጠብቆ ክርስትያኑ ህዝብ እያረደ ቤተክርስትያን እያቃጠለ ሲገሰግስ፤ በዚያ የነበሩት ሊቋቋሙት ባለመቻላቸው ህዝበ ክርስትያኑ የድረሱልኝ ጩሀት ሲያሰማቸው አጼ ምንሊክ ምን ይሰሩ እንደነበር ለጊዜው ልተወውና አጼ ዮሐንስ ግን ሁለት መጥፎ አማራጮች ገጠምዋቸው። ከሁለቱ ባእዳን ወራሪዎች የትኛውን ቅድሚያ መስጠት የሚል። አጼ ዮሐንስ የወሰዱት እርምጃ ሁለቱም ባእዳን ቢሆኑም የሚብሰው ግን ሐይማኖትን የሚያረክስ አብያተ ክርስትያናትን የሚያቃጥል ቅድሚያ መስጠት አለብኝ ብለው በመወሰን መተማ ላይ በጀግንነት ሲያዋጉና ሲዋጉ ሂወታቸውን ማለፉ ማንም ከታሪክ ሊፍቀው የማይችል ዘልዓለም ሲዘከር የሚኖር ሐቅ ነው። ታድያ ሻለቃ ዳዊት አጼ ዮሐንስ ተጠያቂ ሲያደርጉ የትኛው የታሪክ መነፅር ተጠቅመው ይሆን? ወይስ አጼ ምንሊክን ለምን ተነኩብኝ ነው።

ዋናው ዓላማዬ መስመር በመስመር ወይም ምእራፍ በምእራፍ መጽሐፉን መገምገም አይደለም። ታሪክ ሲበረዝ አደጋው ምን ያህል እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው። ስላለፈው በታሪክ መልክ ተዘግቦ ሲቀመጥ ለቀጣይ አንቅስቃሴዎች ትምህርት እንዲሆን ነው። ስለ ኤርትራ በኤርትራዊያን በኩል የሚነገር አለ፤ በኛ በኢትዮጵያውያን በኩልም የሚባል አለ። ዋናው ቁምነገሩ ኤርትራ 50 ዓመት በጣልያን ቅኝ ግዛት፤ 10 ዓመት በእንግሊዝ ሞግዚትነት ቆይታ በሁዋላ ለ30 ዓመታት ከኢትዮጵያ ጋር “ተዋህዳ” ግን መረጋጋት የሌለበት በጦርነት አዙሪት ውስጥ ከኖረች በሁዋላ “ነፃነትዋን” ካወጀች እነሆ 18 ዓመት አስቆጥራለች። ያለፉት 30 ዓመታት ኤርትራ ፍጹም ውህደት

ውስጥ ነበረች ብንል ስህተት ይሆናል። ይብዛም ይነስ ፌዴሬሽን ከፈረሰ በሁዋላ በሁከት ውስጥ ነበረች።
በሆነ ታዓምር ታሪኩ ሌላ ፍጻሜው ሌላ ሊሆን አይችልም። የአሁኑ ውጤት የእውነተኛው የኤርትራ ታሪክ ውጤት ነው። ከአሁን በሁዋላ ኤርትራና ኢትዮጵያ ሊዋሀዱ ከሆነ ያለፈው ታሪክ አሁን እየቀረበ ባለው አቀራረብ ከሆነ ብዙ ውጤት አይኖረውም። ባለፈው ያልሰራ አሁን የሆነ ተዓምር ተፈጥሮ ኤርትራዊያንን አሳምኖ ሊሰራ አይችልም። የሚሰራው ፍቱን መፍትሄ ሌላ ሊሆን ነው።
ስለዚህ ሻለቃ ዳዊት በመጽሀፋቸው ስለ ባንዴራ ክብር ስለ አጼ ምኒልክና ዓድዋ ስለ ኢትዮጵያ ሰራዊት አመሰራረት … ብዙ ሐቆች አስቀምጠዋል። በአንድ መዋእል ግን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚፈጸሙ ስህተቶች አሉ። እነዚህ ስህተቶች በትክክል መቀመጥ ነበረባቸው፤ ምክንያቱም ያስቀመጥዋቸው ሐቆች አካል ናቸውና።

 ዋናው ስጋቴ ሲጀመሩ በግለ ሰብና በቡድን ይሆኑና ቀስ በቀስ የህዝብ አመለካከት ወደ መሆን የሚደረሱ በጣም የተዛቡና አፍራሽ አመለካከቶችን ነው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ ተብሎ ህዝብን ያነሳሳልኛል ያሉትን በሙሉ በቅስቀሳ መልክ እየተጠቀሙበት ነው። ይህ በግለ ሰቦች ይሁን በድርጅቶች እየተሰራጩ ያለው መርዛም ፕሮፖጋንዳ በውል ላጤነው ጤነኛ ሰው ወዴት እያመራ እንዳለ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል። ጥቂቶቹን ልጥቀስ፡
-ትግሬዎች አገራችን እየዘረፉ ናቸው፤
-አገራችን በአናሳ እስከ መቸ ትገዛለች (3 ሚልዮን የማይሞላ ህዝብ እንዴት 80ሚልዮን ህዝብ ያስተዳድራል፤
-ቁልፍ ቁልፍ የመንግስት ስልጣን በትግሬዎች ተያዘ
-ከሁሉም የኢትዮጵያ አከባቢ ለትግራይ ጠቃሚ ነው የተባለው ሁሉ እየተነቀለ ተጓጉዟል
-ትግራይ ውስጥ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ሁሉም ተማሪዎች በኮምፒተር ነው የሚማሩት
-ትግራይ ውስጥ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል የበለጠ ጥራት ያለው ስራዓተ ትምህርት ይሰጣል
-ትግራይ በፋብሪካ ብዛት ልትሰምጥ ናት
-በትግራይ ውስጥ የኤርትራ ግጭት እያመሃኙ ከፍተኛ የወታደራዊ ተቋም እየገነቡ ነው

-ተወዳዳሪ የሌላቸው ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እየተገነቡ ናቸው

-ለመገንጠል ቀድመው የተዘጋጁበት ስለሆነ ሊገነጠሉ ናቸው

-ወያኔና የትግራይ ህዝብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው ፤ ልዩነት የላቸውም

-ወያኔ መወገድ፤ መጥፋት አለበት

ወ.ዘ.ተ……ወ.ዘ.ተ…….ወ.ዘ.ተ……..

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውና ሌሎች ያልጠቀስኳቸውን ደምረን ብናያቸው ወዴት እያንሸራተቱ እየወሰዱን ናቸው። ከግለ ሰብና ከቡድን አመለካከት አልፈው የህዝብ አመለካከት እየሆኑ ናቸው። እነሱ፤ እኛ እየተባባልን እንደህዝብ መፈራረጅ ሲጀመር በማህል ክፍተቱ እየሰፋ ይሄድና አንድነት የምትባለው ማረፊያ ቦታ ይጠባታል ወይም ታጣለች።

አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ የተወሰኑ ቡድን የሚመለከት እንጂ እንዳለ ድፍን የትግራይን ህዝብ የሚመለከት አይደለም። አንድ ሰው ኩላሊቱ ታሞ ሐኪም ጋር ቢሄድና ሐኪሙ ያመመህ ጉበትህ ነው ብሎ መድሃኒት ቢሰጠው፤ ኩላሊቱም አይድንም ጉበቱም በማያስፈልገው መድሐኒት ይመታና ከጥቅም ውጭ ይሆናል፡፤

ለዚህ ነው እውነታ ከተዛነፈ፤ መፍትሄ የምትለውም ይዛነፋል፤ ውጤቱም አፈራሽ ይሆናል የምለው።

ባህሩ